**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: קיץ תשע"ז, 2017

**מספר השאלון: 005374**

**תרגום לאמהרית (6)**

# תורה שבעל פה

בית, חינוך ומשפחה — יחידה לעולים חדשים

## על פי תכנית הרפורמה ללמידה משמעותית

### הוראות לנבחן

א. משך הבחינה: שעה וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה: בשאלון זה שלושה פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | (16x4) | 64 | נקודות |
| פרק שני<br>או:<br>פרק שלישי | (12x3) | 36 | נקודות |
| סה"כ | | 100 | נקודות |

ג. חומר עזר מותר בשימוש: מילון עברי־לועזי / לועזי־עברי.

ד. הוראות מיוחדות: אין.

כתוב במחברת הבחינה בלבד, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב כטיוטה (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).

רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**ב ה צ ל ח ה !**

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ጊዜ፦ የ2017 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 005374**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የቃል መጽሐፍ ቅዱስ

ቤት፣ ትምህርትና ቤተሰብ - ለአዲስ ገቢዎች አንድ ዩኒት

## በሪፎርሙ ትርጉም ያለው የማስተማር ዕቅድ መሠረት

### ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች

א. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ አንድ ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎች ይዟል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | (4x16) | 64 | ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት<br>ወይም፦<br>ምዕራፍ ሦስት | (3x12) | 36 | ነጥብ |
| በአጠቃላይ | | 100 | ነጥብ |

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦ የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. ልዩ መመሪያ፦ የለም።

እንደ ንድፍ (טיוטה) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ የሒሳብ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ። በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (64 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አራቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 16 ነጥብ)።

**1. የትዳር ጓደኛ ማግኘትና ትዳር**

ሀ. ርብቃ ለይስሐቅ ለትዳር የምትስማማው ሴት እሷ እንደሆነች ለማጣራት የአብርሃም ባሪያ ርብቃን ጠየቀ።

(1) ለባሪያው ጥያቄ ከመለሰችው መልስ ለማወቅ የሚቻለውን የርብቃን ሁለት መልካም ባሕሪያት ጻፍ።

(2) የጻፍከው እያንዳንዱ ባሕሪይ በርብቃ ምላሽ ውስጥ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን አብራራ።

(8 ነጥብ)

ለ. በራብ ጽቪ ይሁዳ ኩክ መሠረት ፥ ወንድ እና ሴት የጋራ የሆነ ጉዳይ አላቸው ነገር ግን በወንድ እና በሴት መካከል ልዩነቶችም ደግሞ አሉ።

(1) ለወንድ እና ለሴት የጋራ የሆነው ጉዳይ ምን እንደሆነ ጻፍ።

(2) በወንድ እና በሴት መካከል ለምን ልዩነቶች እንዳሉ አብራራ።

(8 ነጥብ)

**2. የቅርበት (መነካካት) መከልከል ("איסור נגיעה") ኀሰሃ ስለመግባት**

ሀ. በራምባም መሠረት አንዱ ለአንዱ ባልተፈቀዱ በወንድ እና በሴት መካከል ያለ የመውደድ ቅርበት (መነካካት) እገዳ ("ኢሱር ንጊዓ") ከኦሪት የመነጨ ነው። ነገር ግን በራምባን መሠረት ይህ እገዳ ከሊቃውንት ("ሃሃሚም") የመነጨ ነው።

(1) የእያንዳንዳቸውን አቋም አብራራ።

(2) በ"ራብ" አብርሃም ይስሐቅ ሃኮሔን ኩክ (הראי"ה קוק) መሠረት ራምባን ከራምባም ሐሳብ ጋር የሚስማማበት ሁኔታ ምንድን ነው?

(9 ነጥብ)

ለ. (1) .(משלי, כ"ד, ט"ז) "כי שבע יפול צדיק וקם" ("ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜ ይነሣል" ምሳሌ 24 ፥ 16)። በራብ ይስሐቅ ሁትነር መሠረት ፥ ይህ ጥቅስ ሁለት ትርጉሞች አሉት ይኸውም — የአላዋቂ ሰዎች ትርጉም እና የአዋቂ ሰዎች ትርጉም። ለዚህ ጥቅስ የአዋቂ ሰዎችን ትርጉም ጻፍ።

(2) በራብ ይስሐቅ ሁትነር መሠረት ፥ እንዴት "ውድቀትን" መቋቋም እንደሚቻል ዘርዝር።

(7 ነጥብ)

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

**3.** <u>መቼ ነው ማግባት?</u>

**א.** "בן שמונה עשרה לחופה" (אבות, פרק ה', משנה כ"א).
("በአስራ ስምንት ዓመትህ ወደ ሑፓ" ፤ "አቮት" ምዕራፍ 5 "ሚሽኔ") ዛሬ በእኛ ጊዜ ሁኔታው ለምን በሚሽኔ በተገለጸው መሠረት አልሆነም?
<u>ሁለት</u> ማስረጃዎችን ጻፍ። (7 ነጥብ)

**ב.** (1) በ"ራምባም" መሠረት በኦሪት ሥራ ላይ የሚገኝ ሰው ዘግይቶ ማግባት ይችላል ÷ ምክንያቱም "በትዕዛዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ከሌላ ትዕዛዝ የተፈታ/ነጻ ነው"።
የራምባምን ማስረጃ አብራራ።

(2) ነብሳቸውን ይማርና ሊቃውንቶቻችን ሰው ከማግባቱ በፊት ለቤት ወጪው ማሰብ አለበት ብለው ወስነዋል÷ ሆኖም ግን ጥቅሱ
"אישה תארש...בית תבנה... כרם תִטע..." (דברים, כ"ח, ל') ("ሴት ልጅ ታጫለህ... ቤትንም ትሠራለህ... ወይንም ትተክላለህ..." ይላል። ዘዳግም 28 ÷ 30) ነብሳቸውን ይማርና የሊቃውንቶቻችንን ውሳኔ የሚቃረን ይመስላል። በራምባም መሠረት የዚህን ተቃርኖ ሰበብ ጻፍ።

(9 ነጥብ)

**4.** <u>"ኪዱሺን/ቅድስና" እና ጋብቻ</u>

**א.** (1) በዘመናችን ያለው "ማጨት" ምንድን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበረው "ማጨት" ምንድን ነው?

(2) "የታጨ"/"ארוס" እና "የታጨች"/"ארוסה" የሚሉት (የዕብራይስጥ) ቃላት ፊደላቱ በተቃራኒ አቅጣጫ ሲነበቡ <u>የተከለከለ/የታገደ</u> እና <u>የተከለከለች/የታገደች</u> የሚል ፍቺ አላቸው።
"ክልክል" የሚለው ቃል ተቃራኒ የሆኑ ሁለት ትርጉሞች አሉት፦ ግንኙነት/ቅርበት እና ርቀት (קֶשֶׁר וריחוק) የሚሉ።
ከትርጉሞቹ <u>እያንዳንዳቸው</u> በእጮኛሞቹ የእጮኝነት ወቅት እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ አብራራ።

(9 ነጥብ)

**ב.** በሲቪል ሕግ ጋብቻ (בנישואין אזרחיים) የተጋቡት ባለትዳሮች እንደባለትዳር ይቆጠራሉ በሚለው ሐሳብ ላይ በመንፈሳዊያን ሕግ አውጪዎች መካከል በሐሳብ አለመስማማት አለ።

(1) የሲቪል ሕግ ጋብቻ ምንድን ነው?

(2) ባለትዳሮቹ እንደባለትዳር ይቆጠራሉ ብለው የሚገምቱትን የመንፈሳዊያን ሕግ አውጪዎቹን አቋም የሚደግፍ <u>አንድ</u> ሐሳብ <u>ወይም</u> እንደባለትዳር አይቆጠሩም ብለው የሚገምቱትን መንፈሳዊያን ሕግ አውጪዎች አቋም የሚደግፍ <u>አንድ</u> ሐሳብ ዘርዝረህ ጻፍ።

(7 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

5. የመርገም እና መንጻት ("טומאה וטהרה") — እንዳቸው ለእንዳቸው ክልክል በሆኑበት ጊዜ የባለትዳሮቹ አካሄድ

א. (1) አንድ ሰው በመርገም ላይ ካለች ሴት ጋር እንዳይገናኝ የሚለው እገዳ ሰው ከእህቱ ጋር እንዳይተኛ ከሚለው እገዳ ጋር አጠገብ ለአጠገብ/በተነጻጻሪነት በኦሪት የተጻፈ ነው።

ከዚህ አምሳያ (ተነጻጻሪነት) ምን መረዳት እንችላለን?

(2) በመጀመሪያ በመርገም (በወር አበባ) ላይ ላለች ሴት ማጌጥና መቀባባት ክልክል ነው ብለው ነበር በኋላ ደግሞ ይህን እገዳ አንስተውታል።

ለዚህ እገዳ መነሳት/መሠረዝ ምክንያቱ ምን እንደሆነ አብራራ።

(10 ነጥብ)

ב. "סוגה בשושנים" የሚለውን አባባል አብራራ እና በወንድና በሴት መካከል ካለው መራራቅ ፍርድ/ውሳኔ ጋር ያለውን ግንኙነት አብራራ። (6 ነጥብ)

/ገጽ 5 ላይ ይቀጥላል/

**በተማርካቸው ይዘቶች መሠረት ምዕራፍ ሁለትን ወይም ምዕራፍ ሦስትን መመለስ አለብህ።**

## ምዕራፍ ሁለት (36 ነጥብ)

**ከመጽሔቱ ላይ ከ'א - א"י ያሉትን ምዕራፎች ተምረህ** ከሆነ ከ6-9 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 12 ነጥብ)።

**6.** የቤት ውስጥ ባሕል እና በባልና ሚስቱ መካከል ሰላምን መፍጠር

**አ.** (1) ዮሲ እና ሪና ሊጋቡ ነው። በሪና ወላጆች ቤት ያለው ባሕል በዮሲ ወላጆች ቤት ካለው ባሕል የተለየ ነው።
ሪና ከዮሲ ጋር ከተጋባች በኋላ በምን ዓይነት ባሕል ውስጥ መኖር/መኳዝ አለባት? የመንፈሳዊያን ሕግ አውጪዎቹን ሁለት ሐሳቦች ጻፍ።

(2) ለሁለቱ መንፈሳዊያን ሕግ አውጪዎች ዋናው መመዘኛ ምንድን ነው?

(7 ነጥብ)

**ב.** "אלו דברים שאדם אוכל פֵּרותיהן בעולם הזה והקרן קיימת לו לעולם הבא... והבאת שלום".
(פאה, פרק א', משנה א')

በ"ምሽኔ" ያለው አባባል "ሰላምን ማምጣት/"הבאת שלום" እንጂ "ሰላምን ማድረግ"/"עשיית שלום" አይደለም።
በተማርከው ("תפארת ישראל") የራብ እስራኤል ሊፕሺት ትርጉም መሠረት ÷ "ሰላምን ማምጣት/"הבאת שלום" በሚለው አባባል በመጠቀም መማር የሚቻለው ግብረገባዊ ዋጋ ምንድን ነው? (5 ነጥብ)

**7.** የወቅት ትዕዛዝ (מצוות עונה)

**አ.** (1) የወቅት ትዕዘዝ (מצוות עונה) ምንድን ነው?

(2) የዚህን ትዕዛዝ አስፈላጊነት አብራራ።

(8 ነጥብ)

**ב.** በወንድና ሴት እንስሳት መካከል ባለው ግንኙነት እና በባል እና በሚስቱ መካከል ባለው ግንኙነት መካከል ያለውን አንድ ወሳኝ ልዩነት ጻፍ። (4 ነጥብ)

**8.** ፍቺ

**አ.** ፍቺን በተመለከተ የራባችን ጌርሾም ደንብ ምንድን ነው? እናስ ለምን ይህን ደንብ ደነገገ/አወጣ? (4 ነጥብ)

**ב.** (1) በጣም በከረሩ አጋጣሚዎች ሚስት ባሏን አልፈታም በምትልበት ጊዜ የሚሆንን የፍርድ ቤት መፍትሔ ጻፍ።

(2) እስራኤል ሀገር ባለ ሕግ መሠረት፣ ባል ለሚስቱ የፍቺ ፈቃድ ("ጌት") አልሰጥም በሚልበት ጊዜ ሊጣሉበት የሚችሉትን ሦስት ማዕቀቦች ጻፍ።

(8 ነጥብ)

/ገጽ 6 ላይ ይቀጥላል/

**9. አጫጭር ጥያቄዎች**

ከአ - ገ ካሉት ንዑሳን ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን በአጭር በአጭሩ መልስ። (ለእያንዳንዱ ንዑስ ጥያቄ – 4 ነጥብ)።

**ሀ.** የሴት ለወንድ መቀደስ ለምን በቀለበት ይደረጋል? ለዚህ ሁለት ምክንያቶችን ስጥ።

**ለ.** ኢየሩሳሌምን ማስታወስን የሚመለከቱ በሠርግ ሥነ ሥርዓት ላይ የሚደረጉ ሁለት ልምዶችን ጻፍ።

**ሐ.** የመንጻት በውሃ መጥለምን ግዴታ የሚያረጋግጥ አንድ ምክንያት ጻፍ።

**መ.** በትምህርት መጽሐፍ መሠረት ÷ ወላጆችን የማክበር ትዕዛዝ ትረጉም ምንድን ነው?

/ገጽ 7 ላይ ይቀጥላል/

**በተማርካቸው ይዘቶች መሠረት ምዕራፍ ሁለትን ወይም ምዕራፍ ሦስትን መመለስ አለብህ።**

## ምዕራፍ ሦስት (36 ነጥብ)

**ከመጽሐፉ ላይ ከ'א - 'ו , ከ'י - ד"י ያሉትን ምዕራፎች ተምረህ** ከሆነ ከ10-13 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 12 ነጥብ)።

**10.** የቤት ውስጥ ባሕል እና በባልና ሚስቱ መካከል ሰላምን ማስፈን

**አ.** (1) ዮሲ እና ሪና ሊጋቡ ነው። በሪና ወላጆች ቤት ያለው ባሕል በዮሲ ወላጆች ቤት ካለው ባሕል የተለየ ነው።
ሪና ከዮሲ ጋር ከተጋባች በኋላ ምን ዓይነት ባሕል (አካሄድ) ማዳበር አለባት? የመንፈሳዊያን ሕግ አውጪዎቹን ሁለት ሐሳቦች ጻፍ።
(2) ለሁለቱ መንፈሳዊያን ሕግ አውጪዎች ዋነኛው መመዘኛ ምንድን ነው?
(7 ነጥብ)

**በ.** "אלו דברים שאדם אוכל פֵּרותיהן בעולם הזה והקרן קיימת לו לעולם הבא... והבאת שלום".
(פאה, פרק א', משנה א')

በ"ምሽኔ" ያለው አባባል "ሰላምን ማምጣት/"הבאת שלום" እንጂ "ሰላምን ማድረግ"/"עשיית שלום" አይደለም።
በተማርከው ("תפארת ישראל") የራብ እስራኤል ሊፕሺት ትርጉም መሠረት ÷ "ሰላምን ማምጣት/"הבאת שלום" በሚለው አባባል በመጠቀም መማር የሚቻለው ግብረገባዊ ዋጋ ምንድን ነው? (5 ነጥብ)

**11.** ፍቺ

**አ.** ፍቺን በተመለከተ የራባችን ጌርሾም ደንብ ምንድን ነው? እናስ ለምን ይህን ደንብ ደነገገ። (4 ነጥብ)

**በ.** (1) በጣም በከረሩ አጋጣሚዎች ሚስት ባሏን አልፈታም በምትልበት ጊዜ የሚሆን የፍርድ ቤት መፍትሔ ጻፍ።
(2) በእስራኤል ሀገር ሕግ መሠረት፣ ባል ለሚስቱ የፍቺ ፈቃድ (ጌት) አልሰጥም በሚልበት ጊዜ ሊጣሉበት የሚችሉትን ሦስት ማዕቀቦች ጻፍ።
(8 ነጥብ)

**12.** የቤተሰቡ አኗኗር፣ በትዳር ሕይወት መቀራረብና መራራቅ

**አ.** (1) ሊቃውንት ራቢ ኤልኤዘር ቤን አዛርያን በፕሬዘዳንትነት የሥራ ድርሻ እንዲያገለግል ሲለምኑት የመለሰው መልስ ምን ነበር?
(2) በራብ አብርሃም ይስሐቅ ሃኮሔን ኩክ (הראי"ה קוק) መሠረት ከራቢ ኤልኤዘር ቤን አዛርያ መልስ መማር የሚቻለውን መልዕክት አብራራ።
(6 ነጥብ)

**በ.** በመርገም ጊዜ (בזמן הנידה) እና በሰባት የመንጻት ቀናት ("שבעה נקיים") ባልና ሚስት በማራራቅ ሕግ ይታዘዛሉ።
የማራቁ ሕግ ትዕዛዝ ለባልና ሚስቱ ግንኙነት የሚያደርገው አስተዋጽዖ ምንድን ነው? ሁለት ነገሮችን ጻፍ። (6 ነጥብ)

/ገጽ 8 ላይ ይቀጥላል/

**13.** **አጫጭር ጥያቄዎች**

**ከአ - ד ካሉት ንዑሳን ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን በአጭር በአጭሩ መልስ።**
**(እያንዳንዱ ንዑስ ጥያቄ – 4 ነጥብ)።**

**א.** **የሴት ለወንድ መቀደስ ለምን በቀለበት ይደረጋል? ለዚህ ሁለት ምክንያቶችን ስጥ።**

**ב.** **ኢየሩሳሌምን ማስታወስን የሚመለከቱ በሠርግ ሥነ ሥርዓት ላይ የሚደረጉ ሁለት ልምዶችን ጻፍ።**

**ג.** **በትምህርት መጽሐፍ መሠረት ፥ ወላጆችን የማክበር ትዕዛዝ ውጤቱ ምንድን ነው?**

**ד.** "לעולם ידחוק אדם עצמו ויתגלגל בצער... ואל ישליך עצמו על הציבור" (רמב"ם ושו"ע).
**እነዚህን ዐረፍተ-ነገሮች በራስህ አባባል አብራራቸው።**

**መልካም ዕድል!**
መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።

**בהצלחה!**
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך